## የመዝሙር መሳሪያ ታሪካዊ አመጣጥ

### ክፍል አንድ

### መግቢያ

በአብዛኛው ሃይማኖታው የአምልኮ ሥርዓት ወይንም ምሥጋና በውርድ ንባብ ወይንም በዜማ የታጀበ ሲሆን የመዝሙሩም ዜማ በሙዚቃ መሣሪያ የተቀነባበረ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንም ከቅዱስ ያሬድ ጀምሮ በሦስት የተለያዩ ዜማዎችዋ በተለያዩ የሙዚቃ (የመዝሙር) መሣሪያዎች እየተቀነባበሩ ሲቀርቡ ዘመናት ተቆጥረዋል።

ይህን ስለ ሙዚቃ መሣሪያዎች ታሪካዊ አመጣጥ የሚገልጽ አጭር ጥናታዊ ጽሑፍ ማቅረብ ያስፈለጉበት ዋና ዋና ምክንያቶች ከዚህ እንደሚከተሉት ናቸው።

ሀ) ከድሮ ጀምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ምሥጋናዋን ለጌታ በዜማ ለማቅረብ የምትገለገልባቸው ልዩ ልዩ መሣሪያዎች ከየት እንደተገኙ (እንደተወረሱ) ለመግለጽ፣
ለ) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በዜማ የመዝሙር አቀራረብ በተወሰኑ የሙዚቃ መሣሪያዎች ብቻ ተለይተው እንዲቀርቡ (እንዲዘጋጁ) የሚደነገግ ደንብ ወይንም ሃይማኖታዊ ቀኖና ያለ መኖሩን ለማሳየት፣
ሐ) በተለያዩ የሙዚቃ (መዝሙር) መሣሪያዎች አጠቃቀም ረገድ በሀገር ቤትም ሆነ በውጭ የሚኖሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ወጣቶች በኩል እየተንጸባረቀ ያለውን የተሳሳተ አመለካከት ለማረቅና በምትኩም የጠራና ትክክለኛ አቅጣጫ እንዲይዙ ለመረዳት።

### ክፍል ሁለት

### የሙዚቃ (የመዝሙር) መሣሪያዎች ታሪካዊ አመጣጥ

በተለያየ ቅርጽ የተለያዩ የሙዚቃም ሆነ የመዝሙር መሣሪያዎችን የፈለሰፉና ያዘጋጁ ከዓለም የመጀመሪያዎቹ የመካከለኛው ምሥራቅ የፋርስና የባቢሎን የግብጽና የአሦር የሜሶፖታሚያና የሱሜሪያን ሰዎች ናቸው። ለምሳሌ ያህል መሣሪያዎቹም በመጠኑ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል። እነዚህም፥

1. **መለከት** Trumpet
2. **በገና** Harp (Kinnor)
3. **ከበሮ** Tambourine (Timbrel)
4. **አርጋኖን** Organ
5. **ጸናጽል** Sistrum (Cymbal)
6. **መሰንቆ** Lyres (Lyre)
7. **ጊታር** Lute
8. **ቀርነ መለከት** Shophar
9. **ነጋሪት** Castanet

10. **ዕንዚራ** Accordion
11. **ዕምቢልታ** Flute
12. **ዋሽንት** Cornet Sackbut **ናቸው።**

2.1. **በገና ፡-**

**በገና የተሰኘው መሣሪያ አንደኛ ከ 3200 ዓመተ ዓለም ቀደም ሲል በኢራን ደቡባዊ ምዕራብ ቶጋ ሚሽ በተባለ ሥፍራ በሸክላ ላይ፣ ሁለተኛ በ 3000 ዓመተ ዓለም በባቢሎን በመቃብር ሐውልት ላይ ተቀርጾ የ ተገኘ የሙዚቃ መሣሪያ ነው።**

2.2. **ጸናጽል ፡-**

**ጸናጽል የተባለው መሣሪያ ደግሞ የተሠራው (የተፈለሰፈው) በግብጻውያን ሲሆን የተዘጋጀውም አኤሲስን** (ISIS) **በሴት አንቀጽ የምትጠራዋን የግብጽ ጣዖት በዚህ መሣሪያ ለማመስገን በተለያየ ቅርጽ የተዘጋጀ የዝማሬ መሣሪያ ነው።**


2.3. **ኦርጋንን በተመለከተ፡**

**የመዝሙር መሣሪያዎች የተለያየ ቅርጽ ያላቸውና የተለያየ የድምጽ ቃና የሚሰጡ፣ እግዚአብሔርን ለማ መስገን የተዘጋጁ መሣሪያዎች ናቸው። ከእነዚህም መካከል እጅግ ጣዕመ ዜማው የሚማርክና የሚመስጥ አንዱ ኦርጋን ወይንም አርጋኖን ነው። መዘመር የሚለው ቃል ብሉይ ኪዳን ውስጥ** 309 **ጊዜ፣ በሐዲስ ኪዳን ደግሞ** 36 **ጊዜ ተጽፎ ይገኛል።** SEPTUAGINT (**ሰብዐ ሁለት**) **ተርጓዋሚዎች በ** 270 **ዓመተ ዓለ ም አካባቢ ብሉይ ኪዳንን ከእብራይስጥ ወደ ግሪክኛ ሲመልሱ** (**ሲተረጉሙ**) ugab **የሚለውን የእብራይስ ጥ ቃል አርጋኖን ብለው ተረጎሙ። ዘፍ.** 4፡21 **። ኢዮ** 21፡12 **። ኢዮ** 30፡31 **። መዝ** 150፡4 R.S.V(Revised Standared Version)

**ደግሞ** ... **በማለት ተርጉሞታል። መዝ** 150፡4 **በታላቁዋ ብሪታኒያ የታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ አርጋኖንን ዛጉፍ በማለት ተርጉሞታል።**


**አርጋኖን የግሪካውያን፣ የሮማውያን፣ የኦሪየንታል፣ የእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በመዝሙር መሣ ሪያነቱ የሚጠቀሙበት ጣዕም ያለው መገልገያ ነው** ፡ (Dictionary of Rel.Kn. volume III P.1792; 1883)

**በቅዱስ ያሬድ የዜማ መጽሐፍትና በልዩ ልዩ ገድለ ቅዱሳን ድርሰት ሁሉ አርጋኖንን በብዛት ተጠቅሶ እና ገኘዋለን። ወሶበ ቀርቡ፣ ወበጽሑ ኀበ ሀገረ ስምዑ ድምፀ አርጋኖን ወመሰንቆ፣ ወብዕዛ፣ ወይቤሉ ምንትኑ ዝንቱ** ... **ትርጉሙ - ወደ ሠፈርም በደረሱ ጊዜ የመሰንቆንና የአርጋኖንን፣ የዕምቢልታንም ድምጽ ሰምተ ው «ይህ ነገር ምንድነው? ተባባሉ» በአቅርንት ወብዕዛ፣ አርጋኖን ወብዕዛ። ቃለ ቀርን ወዕንዚራ፣ ወመሰ ንቆ ወብዕዝ ማኅሌት። ወምስሌሁ መዘምራን እለሂ በጸናጽል፣ ወእለሂ በከበሮ፣ ወእለሂ በብዕዛ ወበአቅር ንት። ትርጉም፡- በመለከትና በዕምቢልታ፣ በአርጋኖን፣ በቀርነ መለከትና በዕንዚራ፣ የማኅሌት መሣሪያ በ ሆነው በመሰንቆና በዕምቢልታ፣ ከዚህም ሁሉ ጋር በጸናጽል፣ በከበሮ፣ በዕምቢልታና በቀርነ መለከት ይዘ ምሩ ነበር። 2ኛ ዜና 13፡12፣ 15፡14፣ ዳን 3፡5፣ 2ኛ ሳሙ 6፡5። መስከረም 18 ቀን ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ገጽ 277።**



ኦርጋኖን


## 2.4. መሰንቆ፣ በገና፣ ጊታርና ዕምቢልታ



ቀርን መለኮት፤ በታላላቅ በዓላት የሚነፋ ፤ ሕዝብን
ወደ ምኩራብ፤ ወደ ቤተክርስቲያን የሚሰበስብ



የአሶራውያን መሰንቆ፤ የአሦር ሰው
መሰንቆ ሲጫወት ያሳያል።



እንዚራ



የአሦራውያን ከበሮ፤ በጠፍርና በቆዳ የተጠፈረና የተጠረዘ

የግብጽና የፋርስ፣ የባቢሎንና የአሦርያ ሙዚቃ ረዘም ያለ ታሪክ ያለው ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ 3200 ዓመተ ዓለም ቀደም ሲል የነበረ ሲሆን ይህም የመካከለኛው ምሥራቅ የሙዚቃ መሣሪያ በየደረጃው ለ ብሉይ ኪዳን ሰዎችና ለሩቅ ምሥራቅ ሰዎች መሰረት ሆኖአል።
ከመዳብና ከብረት የተሠሩ መሰንቆና በገና፣ ጊታርና ዕምቢልታ እንዲሁም መለከት ከቱታንከሜን (TUTA NKAMEN) መቃብር (1237-1338...) የተገኙ ናቸው። እንደዚሁም በብር የተሠሩና የተጌጡ ዘጠኝ መሰንቆ ዎችና አርጋኖኖች (ኦርጋኖች) በባሕል የአብርሃም ሀገር እየተባለ ከሚነገረው በኡር በንገሥታቱ የመቃብር ቦታ በተለይም ቱአቢ ለምትባለዋ ንግሥት ለርስዋ ክብር ሲባል ከዚህ ዓለም በሞት በተለየች ጊዜ ከርስ ዋ አስከሬን ጋር ገረዶችዋ ከነነፍሳቸው በተቀበሩበት ቦታ በ 2650 ዓመተ ዓለም የተገኙ ናቸው።

በብሉይ ኪዳን ሌዋውያን ካህናትም ሆኑ ሌሎች በበገና፣ በመሰንቆ፣ በእንዚራ፣ በከበሮ ወዘተ ይጫወቱ የ ነበረ ሲሆን እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የሙዚቃ መሣሪያዎች የተወረሱት (የተዋሱት) ከጎረቤቶቻቸው ከፋ ርስ፣ ከባቢሎን፣ ከአሦርና ከሚስፖታሚያ ወዘተ እንጂ የእነርሱ አይደሉም። ስለዚህ ዩባልና ልጆቹ በበገ ናም ሆነ በተለያዩ መሣሪያዎች ሲጫወቱ የመጀመሪያዎቹ ቢሆኑም (ዘፍ 4፥25) ለመሣሪያዎቹ ቅርጽና መ ልክ የሰጠው ዳዊት ነው (1010-970 B.C)። ዳዊት የሃዘንም ሆነ የደስታ መዝሙር ደራሲ በመሰንቆና በበገ ና ተጫዋችነቱ የሚነገርለት ሲሆን (አሞ 6፥5፣ 1ኛ ሳሙ 16፥16-18) ከዳዊት በፊት የነበረው የመካከለኛ ው ምሥራቅ የሱማርያን (ኡር) ንጉሥ ሹልጊ (2093-2045B.C) ግን ይበልጥ እንደነበረ ይነገርለታል።

The literary record of David’s many abilities is foreshadowed only by that of Sumerian King Shulgi of Ur (2093-2045 B.C.), who celebrated his own remarkable talents in music, athletics, and statesmanship in a number of finely crafted hymns. (HARPER’S BIBLE DICTIONARY. PP.668.1985. LONDON).

በግብጽና በግሪክ በሮምና በመካከለኛው ምሥራቅ የጣዖት ማምለኪያ በነበሩበት ቦታዎችና በጣዖታት አጽ ም ላይ አብያተ ክርስቲያናት ታንጸው ዛሬ 24 ሰዓት የእግዚአብሔር መመስገኛ ቦታዎች እንደሆኑ ሁሉ እንዲሁም ለጣዖት የመዝሙር መሣሪያዎች የነበሩት ሁሉ አሁን ደግሞ ለእግዚአብሔር የማኅሌት መሣሪ ያዎች ሆነዋል። ለዚህም ማስረጃ ሰኔ 12 ቀን የሚነበበውን ስንክሳር መመልከት ይቻላል።

## ክፍል ሦስት

## <u>የመዝሙር (የሙዚቃ) መሣሪያዎች አጠቃቀም</u>
## <u>በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን</u>

ኢትዮጵያ የክርስትና እምነትን ከመቀበልዋ በፊት ጁዴይዝምን (ኦሪትን-ቶራን) ተቀብላ ለዘመናት በአንድ አምላክ ታመልክ እንደነበር የተለያዩ የታሪክ መጻሕፍትን በአስረጅነት ለመጥቀስ ይቻላል። ከዘመነ ብሉ ይ ጀምሮ ያሬድ እስከ ተነሳበት እስከ አፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት (515-529) ድረስ በምኩራብ ም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ይፈጸም የነበረው የምስጋና አቀራረብ በውርድ ንባብ እንጂ በዜማ አልነበረም።

በኢትዮጵያ በዜማ ማመስገንና መዘመር የተጀመረው ቅዱስ ያሬድ የዜማ ዓይነቶችን በሦስት የአዘማመር ስልት መድቦ ከደረሰ በኋላ ነው። እርሱም ዕዝል፣ግዕዝና አራራይ ይባላሉ። የቅዱስ ያሬድ ዕረፍት ግን ቦት 11 ቀን ነው። ለእርሱ መታሰቢያ ከአንድ ደራሲ በተደረሰው ምልጣን ላይ እነዚህን ሦስቱን የያሬድ

የዜማ ዓይነቶች ደራሲው እንዲህ በማለት ገልጧቸዋል። «ኢየዐዱ እንስሳ ወሰብእ እምነ ሠላስ ዜማሁ»፣ ትርጓሜውም የሰውም ሆነ የእንስሳ ዜማ ከሦስቱ የያሬድ የዜማ ዓይነቶች አያልፍም ማለት ነው።

ከላይ ከክፍል ሁለት እንደተመለከተው በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለያሬዳዊ ዜማ የምትገለገልባቸው እንደ ጸናጽል፣ ከበሮ፣ ነጋሪት፣ አርጋኖን፣ ቀርነ መለከት ወዘተ... ከ3000 ዓመተ ዓለም በፊት ከግብጽና ከፋርስ ከባቢሎንና ከአሦር የተገኙ ናቸው። በአጭር አገላለጽ የሙዚቃ መሣሪያዎች አመጣጥና አመሠራረት ከመካከለኛው ምሥራቅ ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እንደሌሎቹ የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ሁሉ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ወርሳ ለረጅም ዘመናት ስትገለገል የቆየች ሲሆን እነዚህ መሣሪያዎች ብቻ የውዳሴ፣ የዝማሬ ማቅረቢያ እነዚያ ደግሞ ለውዳሴም ሆነ ለዝማሬ መገልገያነት አይውሉም የሚል የሙዚቃ (የመዝሙር) መሣሪያዎችን አጠቃቀም የሚያብራራ ቀኖና ወይንም ደንብ የላትም። በኦርጋን መዘመር መናፍቅነት ነው፣ በከበሮና በጸናጽል መዘመር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የጥንታዊነት መለያ ነው የሚለው አመለካከትና ሃሳብ ከላይ እንደተገለጸው ሁሉ ታሪካዊ መሠረት የሌለው ነው።

በኦርጋን መዘመር ክልክል ነው የሚሉ ሁሉ እጅግ ተሳስተዋል። ምክንያቱም የቅዱስ ያሬድን የዜማ መጽሐፍ፣ <u>አርጋኖነ ድንግል ማርያም</u> የተሰኘውን የቅድስት ድንግል እመቤታችንን የምሥጋና መጽሐፍ፣ መጽሐፍ ስንክሳርን እና ባጭሩ የብሉይ ኪዳንን መጽሐፍትን ያላዩና ያላነበቡ ናቸው ለማለት ያስደፍራል።

<u>ኦርጋን</u>፥- በግሪክኛ ኦርጋኑን፣ በላቲንኛ ኦርጋኑም፣ በግዕዝ አርጋኖን ይባላል። ትርጉም፥- የማኅሌት ዕቃ፣ መዝሙር፣ በገና፣ ውዳሴ፣ ምስጋና፣ መልካም ዜና፣ ለጆሮ፣ ለልብ የሚጣፍጥ፣ ደስ የሚያሰኝ ድምጽ። አጽንአ አውታረ አርጋኖን፣ አርጋኖን ወብዕዛ። አርጋኖነ ማርያም ድንግል። (አዋል ስንክሳር፣ መስከረም 18 ቀን፣ አርጋ. 1 ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት፣ 1948 ገጽ 239)።

ቅዱስ ያሬድ በዜማ መጽሐፍ 1ኛ አርጋኖን፣ 2ኛ እንዚራ፣ 3ኛ መሰንቆ ለማኅሌተ እግዚአብሔር ታላቅ መሣሪያዎች መሆናቸውን ከዚህ እንደሚከተለው ይገልጻል።

1ኛ. አስተጋብአተነ ቤት፣ እስመ ለዓለም፥- ሰባኬ ወንጌል ዮሐንስ <u>አርጋኖነ</u> ማኅሌት ዘይደምፅ ለቤተ ክርስቲያን ቀርነ ነባቢ ዘይጼውዕ መሐይምናነ ... ትርጓሜው፥- ወንጌልን የሚሰብክ ዮሐንስ ድምጹም በቤተ ክርስቲያን የሚጣፍጥ የማኅሌት አርጋኖን ነው። ዮሐንስ እንደ ቀርነ መለከት ምእመናንን ወደ ቤተ ክርስቲያን ይጋብዛል። (ከዘመነ ልደት ድጓ ጥር 4 ቀን የሚዘመር)
2ኛ. አማኅኩኪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከብካብ ኮነ በቃና ዘገሊላ <u>ዕንዚራ</u> ደምፀ በዉስተ ጽርሕ... ትርጓሜው፥- ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሆይ እኔ እሰግድልሻለሁ። ክርስቶስ በቃና መንደር ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ በለወጠ ጊዜ ያደረገውን ተአምር እያስታወስሁ በእንዚራ በመቅደሱ እዘምራለሁ። (ከዘመነ ልደት/ አስተርእዮ ድጓ፣ በሰንበተ ክርስቲያን ብቻ የሚዘመር፣ ምድቡ ከመወድስ ክፍል)።

3ኛ. ሥረዩ ቤት፣ በሁለት፣ አቡን፣ ስብሕ ወኃይልክ ወኢትምሀክ ቃለከ ማዕነቅ ተስምዐ በምድርነ ዮሐንስ ኒ ይቤ ከመ ዕንዚራ ዉስተ ጽርሐ ንጉሥ። <u>ትርጓሜ</u>፥- በፍጹም ኃይልህና ድምፅህንም ሳትቆጥብ እግዚአብሔርን አመስግን። መስከረም ስለጠባ ቁራውም በምድራችን እየዘመረ መጣ። ዮሐንስም ይህ መዝሙር በንጉሡ አዳራሽ በእንዚራ እንደሚዘመር ዓይነት ነው ይላል። (ከዘመነ ጽጌ ድጓ፣ ከዘወትሩ አቡን)።

4ኛ. ደብተራ ፍጽምት ዘጳውሊ ለማኅደሩ ዘጽድቅ ዘገብራ ከሃሌ ፈለስት እምዘይበሊ ኀበ ኢይበሊ <u>በመሰ ንቆሁ</u> እንዘ የሃሊ ዳዊት አቡሃ ዘወልዳ ወዓሊ። <u>ትርጓሜ</u>፥- ቅድስት ማርያም ከሚያልፈው ዓለም ዳዊት በመሰንቆው እየዘመረላት ሳለ ነፍስዋ ከሥጋዋ ተለይታ ወደማያልፈው ዓለም ሄደች። (እግዚሐር ነግሥ፣ ከዘመነ ክረምት ድጓ፣ የእመቤታችን፣ ነሐሴ 16 ቀን)።

5ኛ. ሃሌ ሉያ ለአብ ንሴብሕ ከመ ቀስተ ደመና ዘአሜ ክረምት አክሊል ንጹሕ ዲበ ርዕሶሙ ሃሌ ሉያ ለወልድ ንዜምር ሃሌ ሉያ ወለመንፈስ ቅዱስ ንሴብሕ ወንዜምር ኪያሁ መድኅነ ከመ ዝበጠተ <u>መሰንቆ አ ርጋኖን</u> ስብሐቶሙ ለእሙንቱ ካህናት። <u>ትርጉም</u>፥- እንደ ክረምት ቀስተ ደመና ንጽሕ አክሊልን ለካህናት ያዘጋጀ እግዚአብሔር አብን፣ እግዚአብሔር ወልድንና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን እናመሰግናለን። ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡበት የካህናት ምሥጋናም በመሰንቆና በአርጋኖን እንደሚዘመር መዝሙር ጣዕ መ ዜማው ማራኪ ነው። (ከጾም ምዕራፍ የማክሰኞ አርያም)።

## ክፍል አራት

## <u>የማጠቃለያ ሃሳብ</u>

እግዚአብሔርን ለማመስገን በተለያዩ የሚዚቃ (የመዝሙር) መሣሪያዎች መጠቀምና ሌሎችን ማግለል በ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የዝማሬና የዜማ ታሪክ ውስጥ እስከዛሬ አልታየም። ባህሮ ችና ዓሣዎች፣ ተራሮችና ኮረብቶች፣ ፀሐይና ጨረቃ፣ በረዶና ጉም በምድር ውስጥ የሚበቅሉ ሁሉ እግዚ አብሔርን ያመሰግኑታል። (ከቅዱስ ያሬድ ድጓ፣ ስረይ ይትፌሳህ ሰማይ፣ የፋሲካ መዝሙር፣ ጸሎተ ሦስ ት ደቂቅ 3፥57)።

በዚህ አጭር ጥናታዊ ጽሑፍ ውስጥ ለማሳየት እንደተሞከረው ኦርጋኑ፣ ጸናጽሉ፣ ከበሮው፣ ነጋሪቱ፣ ዕን ቢልታውና እንዚራው ወዘተ..፣ የመካከለኛው ምሥራቅ ሰዎች እንጂ የእኛም ሆነ የእብራውያን ቅርስ አይ ደለም። ሁላችንም ከነርሱ የወረስናቸው ሲሆኑ፣ ከበሮውና ጸናጽሉ፣ በገናውና ዋሽንቱ የኛ ነው፣ ነገር ግን ኦርጋኑና እንዚራው ወዘተ የሌላ ነው የሚለው አመለካከት ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ የሚያንደረድር ነው።

ይኸኛው የመዝሙር መሣሪያ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የዜማና ዝማሬ ይወክላል ሌላኛው የሙዚቃ (የመዝሙር) መሣሪያ ደግሞ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች የሚገለገሉበት ስለሆነ በመሣሪያው መጠቀም አይገባንም የሚለው አስተሳሰብ ኢሎጂካዊ ነው። በሌላ አነጋገር ከላይ የተጠቀሰ ውን አስተሳሰብ ማራመድ ይኸኛው የሃይማኖት ዘርፍ ያዘጋጀውን መጽሐፍ ቅዱስ አናነብም፣ እነርሱ የነ ኩትን አልነካም ወዘተ... ወደሚለው ድምዳሜና አንድምታ የሚያመራ ሲሆን የእውቀትና የብስለትን የሚ ያንጸባርቅ ነው።

የሙዚቃ መሣሪያዎች ታሪካዊ አመጣጥን አስመልክቶ በቀረበው በዚህ እጭር ጥናታዊ ጽሑፍ ውስጥ የ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ ምሥጋናዋን ለእግዚአብሔር ለማቅረብ የም ትገለገልባቸው እንደ ጸናጽል፣ ከበሮ፣ ነጋሪት፣ አርጋኖንና፣ ቀርነ መለከት ወዘተ የመሳሰሉት ከየት እንደ ተወረሱ፤ እንዲሁም በዜማ የመዝሙር አቀራረብን በተመለከተ በተወሰኑ መሣሪያዎች ብቻ መገልገል እን

ዳለብን የሚደነግግ ሃይማኖታዊ ቀኖና አለመኖሩን በሚገባ ለማብራራት ተችሏል። በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ
ከተገለጸው ታሪካዊ ትንታኔ በተለየ መልኩ በቅርቡ በቅርብ ዓመታት ወዲህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እምነ
ት ተከታይ በሆኑ አንዳንድ ግለሰቦችና ቡድኖች አማካኝነት የሙዚቃ መሣሪያዎችን በሁሉት በመፈረጅ የ
ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የምሥጋና መዝሙሮች መቅረብ ያለባቸው ጥንታዊና ለያሬ
ዳዊ ዜማዎች ተስማሚ በሆኑ በእነዚህ መሣሪያዎች ብቻ መሆን አለበት። ነገር ግን በሌሎቹ መገልገል ጥ
ንታዊነትንና ያሬዳዊ ዝማሬን አይወክሉም የሚለው አመለካከት ወጣቱንና ታዳጊውን ትውልድ በማሳሳትና
በማደናገር ላይ ይገኛል። ስለሆነም ታሪካዊ ማስረጃዎችን ዋቢ በማድረግ የተጠናቀረው ጥናታዊ ጽሑፍ
በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በተሳሳተ ጎዳና በመራመድ ላይ ያሉትን ወገኖች ግንዛቤያቸውን ሰፋ እንዲያደር
ጉ እገዛ ያደርጋል።

መሪጌታ(ቀሲስ) ጸሐይ ብርሃኑ